# ሞተ አትበሉ !

**እነሆ!**

የምድረ ኢትዮጵያ አንፀባራቂ

የአህጉረ አፍሪካ ተወርዋሪ ኮከብ

ጠለቀ፤

ከድህነት

ኋላ ቀርነት

ሥራ አጥነት ጋር ሲታገል – ሲጥል፣

ጦርነት ሲገጥም – ሲቋጭ በድል፣

ከስንቱ – ስንቱ – ስንቱ – ጋር ሲፋለም – ሲጥል፣

ልማቱን ሲያቀጣጥል –

ወደቀ ፡፡

ምን ወደቀ ይባላል?

ወደቀ 'ሚባል – ወድቆ 'ሚቀር፤

ሞተስ 'ሚባል – ሞቶ 'ሚቀበር ፡፡

ሞተ ብለን፡ –

ማቅ ለብሰን – አመድ ነስንሰን – ስናዝን

ሞቶ ያለ፣

እልፍ አእላፍ ሐውልታትን በቁሙ

ከመቃብሩ በላይ የተከለ፣

ሳይጠፉ 'ሚያበሩ ሚሊዮን ችቦዎችን

ያቀጣጠለ፣

እንደ ማለስ ማን ታዬ?

እንደማለስስ ማን አለ ?

ሞተ አትበሉ

አሁንም አለ፡፡

ለኢትዮጵያ ዕድገት – ለአፍሪካ ልዕልና

ለዓለም ሰላም ፤

ሲያስብ – እረፍት የለም፣

ሲታገል – መታከት የለም፣

ያሰበውን ለማሳካት – እንቅልፍ የለም፣

እንዲህ ዓይነት መሪ – አልታየም ባለም፡፡

የምዕተ ዓመታት የሀበሻ ሕዝብን ሕልም የፈታ፣

የመላ አፍሪካ ትንታግ እንደበት – ጠበቃና አለኝታ፣

ክቡር ራዕይ በሞት ’ማይሸነፍ – በመቃብር ’ማይረታ፣

መሆኑን እያወቃችሁ፣

ለምን ሞተ ትላላችሁ?

መች ረፍት ያውቃልና – አረፈ ትላላችሁ፣

ሞተ ተብሎ ’ንኳ ታምር ሲሠራ እያያችሁ?

ሁለገብ

የልማት – የዕድገት – የሰላም – የዴሞክራሲ መምህር፤

አፍርቶማ እልፍ አዕላፍ ደቀ መዝሙር፤

ሞተ አትበሉ፡ –

ሞትን አሳፈረ ’ንጂ መቼ ሞተ?

ሊቀበር ነው አትበሉ ፡ –

የመቃብርን ልሳን ሊዘጋ ’ንጂ – መች ተቀበረ?

የሚታሰበውን የተገበረ፤

የሚደፈረውን የደፈረ ፤

በልባችን ውስጥ እየዋለ፤

በልባችን ውስጥ እያደረ፤

ለዘላለም ይኖራል ’ንጂ

የኢትዮጵያን ትንሣዔ እንዳበሠረ፡፡

ሞተ አትበሉ

አሁንም አለ፡፡

ሱራፌል ናሆም

ነሐሴ 20 ቀን 2004